# እኔ ታዛቢ ነኝ ያነ ነው ደንበሩ

“ያልረባ ጎጆዬ ቤቀርም ግድ የለኝ፤
እናቴም ልጅ የላት፣ እኔም ወንድም የለኝ።
ሲሰድቡት ዝም ያለ፤
ሲመቱትም ያው ነው።
[ተው አትሻገሩ] እሱ፣ እሱ ነው ደንበሩ
እንዳታሰኙኝ እነማን ነበሩ።” … ወዘተ (ከ ህዝብ ድህረ ገጽ የተገኘ)

ላልበላነው እዳ ከፈሉ እይሉ፤
ይግባኝ እንዳንጠይቅ
ሕግ የለ ባገሩ።
ውጊያ አልፈልግም ለሚል ወገን ሁሉ
እስኪ ልጠይቃችሁ፤
ምን ይሁን ፍትሁ?

መንግሥት አለ እንዳልል
መብት አስጠባቂ አንድም አላየሁም፤
ከማቀጨጭ በቀር ገንቢም አልሰማሁም።
ከፋኝ ሲል ገበሬው አሸባሪ አንተ ነህ
ብሎ ያወግዘዋል፣
ጠረፍ ጠባቂውን “ነፍጠኛ አማራ”
ብሉ እንዲሰደብ ነጋሪት ይመታል።
ሰው ባገሩ እንዲህ እንዲሰደብ
ጭራሽም እንዲጠላ ያቁራል በክልል፤
ሰንደቅ አላማንም ጨርቅ ነው ይለዋል
አንዴት አፌ ደፍሮ መንግሥት አለ ለበል?
ሰወች እንዲጠሉ፣ እንዲህ ካስነገረ፣
እንዴት ሰውስ አይከበር በገዛ አገሩ፣
ከተወነጀለም ሰው ያለመግባሩ፤
እኔስ ሰልችቶኛል ማለት እሹሩሩ።

"ሰው በወንዙ፣ ሰው ባገሩ፣

ቢበላም እሳር፣ ቢበላም፣ መቅመቆ፤

ይከበር የለም ወይ ሰውነቱ ታውቆ።"

ባንዴራውን ሳይቀር ጨርቅ ነው በማለት

ፍጽም አዋርዶታል፣

ገበሪንም በትር ለምን ያዝህ እያለ

በጥይት ይቆላል።

መንግሥት አለ እንዳልል

ትንሽ ትልቅ፣ ውንድ እሴትን ሳይለይ፤

በጥይት ይጠብሳል፣

አንዴት አፌ ደፍሮ መንግሥት አለ ለበል?

አረ ባላህ በሉ ውይንም በየሱስ፤

እስከመቸ ድረስ እንዲህ እንታመስ?

ተው አትከልክሉኝ እኔ ላልቅስለት

ለሆነው የቁም ሙት

ወንድሙን ሲገድል እራሱን በመጥላት፤

ከጡጦ በስተቀር አያውቅ የናቱን ጡት።

ባህልንም አያውቅ እንዳላስመከረው፤

የሱ ሙዚቃ ባህል የጥያት ድምጽ ነው።

ተው አትከልክሉኝ እኔ ላልቅስለት፤

ለሆነው የቁም ሙት።

© ለምለም ፀጋው፣ ንሐሴ 1፣ 2008 (August 8, 2016

በሰሜን በደቡብና በመካከለኛው ኢትዮጵያ ብሶታቸውን በሰላማዊ ሰልፍ ስለገለጹ በመንግሥት ለተገደሉና ለርሃብ ለተዳረጉ ሁሉ መታሰቢይ ይሁን።